Finote Ethio-Canadian Information Centre In Toronto
ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ
1910 Kennedy Road, Unit 3, P. O. Box 417, Toronto, ON, M1P 2L8 E-mail:

# መግለጫ : ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የማጥፋት ዘመቻ መቆም አለበት!

ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት የውጭ ወራሪዎችና ታሪካዊ ጠላቶቿ በወረራም ሆነ በተዘዋዋሪ በውስጥ የጠላት ተገዢዎች ጥቃት ደርሰውባታል፡፡ ሁሉንም ወረራዎችና ጥቃቶች ጀግናው ሕዝቧ ተፋልሞ ለብዙ ሺ ዓመታት አስከብሯት ቆይቷል፡፡ ጠላቶቿ በተነሱ ቁጥር ሕዝብዋ አንድ እየሆነ መመከቱ አልበገሬ ስላደረጋት የውጭ ጠላቶቿ ጥርስ ነክሰውባት ለብዙ ጊዜ ሲያደቡ ቆይተው በመጠኑም ቢሆን የተሳካላቸው የሚመስለው ከሃዲ እና ባንዳ በሆኑ ልጆቿ አማካኝነት ውስጥ ለውስጥ በተደረገው የረዢም ዘመን ቡርቦራ የመከፋፈል አደጋው ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ለሕልውናዋ እጅግ አደገኛ ሁኔታ ላይ መድረሱን እያየን ነው፡፡

እነ አሜሪካና ሌሎችም የምዕራባውያን አገሮች በነደፉትና በገዟቸው ባንዳዎች አማካኝነት 'ነጻ አውጭ" በሚል ስያሜ ላላፉት 50 እና 60 ዓመታት የተሰለፉት እነሻዕቢያ፣ ትሕነግ እና ኦነግ (የኤርትሪያ ነጻ አውጭ፣ የትግራይ ነጻ አውጭ፣ የኦሮሞ ነጻ አውጭ ወዘተ … እያሉ ራሳቸውን በሚጠሩ የጠላት መሳሪያዎች በኩል ጠላት ስራውን እየሰራ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን እያጠፉ ይገኛሉ፡፡

እነዚህ 'ነጻ አውጭ" የተባሉት ባንዳ ቡድኖች ኢትዮጵያን ለማጥፋት በቅድሚያ ዋና መሰረቷ የሆኑትን አማራን ና ኦርቶዶክስ ሀይማኖትን ማዳከም፣ መከፋፈል እና ማጥፋት አለብን በማለት የጥፋት ኢላማ አድርገው ከተነሱ አያሌ አመታት አለፉ፡፡ ለመሆኑ አማራ ኢትዮጵያን ከመገንባትና ከመጠበቅ ውጭ ምን አጠፋ? የኦርቶዶክስ ሃይማኖትስ ማንን በደለ ማንንስ አጠፋ? ለጠላት ወራሪ እንዳይገዛ ከመገዘትና ለሃገሩ በጽናት እንዲቆም ከማስተማር ውጭ? ሆኖም ግን በጣልያን ወረራ ጊዜ የተጀመረው አማራን እና ኦርቶዶክስን ሀይማኖትን የማጥፋት ዘመቻው እነ ትሕነግ እና ኦነግ በሽፍትነታቸውም ጊዜ ሆነ ስልጣን በጉልበት ይዘው በሚገዙበት ወቅት ሕጋዊ ሽፋን ሰጥተውት አማራን በዘር ማጥፋት ግድያና ዘመቻ፣ ከሚኖርበት በማፈናቀልና በማሳደድ፣ በማስራብና በኢኮኖሚ ራሱን ችሎ እንዳይኖር በማድረግ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የአማራው ሕዝብ አልቋል፣ ተፈናቅሏል ስቃዩን እያየ ይገኛል፡፡ የዘር ማጥፋት ግድያውን "ግጭት" እያሉ በመደበቅ በወለጋ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በአርሲ፣ ሀረርጌና ሸዋ እያለቀ እየተሳደደ ይገኛል፡፡ በተለይም የኦነግ ብልጽግና አገዛዝ ጊዜ ተባብሶበት ይገኛል፡፡ ኦነግ ከተዳከመበት እና በግዞት ከቆየበት ኤርትርያ አምጥተው በይፋ በመንግስት መዋቅር ወስጥ በማስገባት እና መከላከያውን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የኦነግ ሰራዊት አድርገው አማራውን እየጨፈጨፉት ይገኛል፡፡ አማራው ራሱን ለመከላከል ሲነሳ እንደወንጀለኛ በመቁጠር እያሳደዱትና በየምክያቱ እስር ቤት ወስጥ ያጉሩታል ደበዛውን ያጠፉታል፡፡ የአማራ ሆዳምና ባንዳም መሳሪያ ሆኖ ይገለገሉበታል፤ ይጠቀሙበታል ቀኑ ደርሶ እስኪያጠፉት ድረስ፣ ምዕራባውያንም የአማራውን ሕዝብ እልቂት 'አልሰማንም አላየንም' በማለት ላሉት ዘረኛ እና ሕዝብ ጨፍጫፊ ቡድኖች መሉ ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ሰሚ ያጣ ጨኸት ሆነ የአማራ ህዝብ እልቂት!

የኦርቶዶክስ ሀይማኖት የጥፋት ዘመቻ የተጀመረው ወያኔ ስልጣን እንደያዘ በነታምራት ላይኔ በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ ሾመው ሕጋዊ ፓትርያርኩን ስደተኛ ካደረጉ ጀምሮ እየቀጠለ የመጣ ጉዳይ ዘሬ የኦርቶዶክስ ሲኖዶስ በመንግስት እውቅናና ድጋፍ የኦሮሞ ቤተክህነት በማለት ከፍሎ እጅግ አደገኛ የሆነ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሆነው ኦርቶዶክስን አስታረቅሁ በሚለው ቁጥር አንድ አጭበርባሪውና ከሃዲው አነጉ አብይ አህመድ መሪነት እነሽመልስ አብዲሳ ፣ አዳነች አቤቤ አማካኝነት ኢትዮጵያን ሊያጠፉ የሚችል አደገኛ የጥፋት ሰራ ነው፡፡ ክህደትና ድርጊታቸውን በጽኑ አውግዞ ለፍርድ ልናቀርባቸው ይገባል፡፡ አብይ አህመድ አሊ ለውጥ አመጣሁ ባለበት ጊዜ እውነት መስሎት የደገፈው 90 በመቶ መካከል አማራውን እና ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዩ ነበር፡፡ እርሱ ግን የሚያጠፋቸውን ሕዝብና ተቋም በቅርብ ርቀት መጥፋታቸውን የሚቆጣጠርበት መንገድ ነበር አዘጋጅቶ አድብቶ ማጥፋት የጀመረው፡፡

ሰለሆነም ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነት ለማጥፋት በቅድሚያ መጥፋት አለባቸው ያሏቸው አማራውና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዩ ዋና ጠላቶቹ ወያኔና ኦነጉ አብይ አህመድ በመሆኑ በአንድነት በመቆም እራሱን እና ጥንታዊ ሃይማኖቱን ለማዳን ቆርጦ መነሳትና ጠላቶቹን ተገቢውን ቅጣትና እና ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል! ሌላ መንገድና አማራጭ የለውም፡፡ አበቃ!

ዘሬ በአማራውን እና ኦርቶዶክሱ የተጀመረው ነገ ደግሞ በሌሎቹ ላይ መድረሱ አይቀሬ ነውና ትሕነግ እና ኦነግ ከነግሳንግሱ ጠራርጎ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ማውረድና ፍርዳቸውን እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፡፡ ካመነታ፣ ጊዜ ከሰጠ ላንዴም ለመጨረሻውን መጥፊያው ቅርብ ነውና ለሕልውናው ሲል በቆራጥነት በአንድነት መነሳት አለብት! ጊዜው አሁን ነው፡፡

በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያለው ሕዝብ አማራውን እና ኦርቶዶክስ ሃይማኖቱን ሕልውና ለማዳን ከተነሳ ለሁሉም ዜጋ እና ሃይማኖት አገር የሆንችውን ኢትዮጵያን ያድናል፡፡ ለዚህም የተቃውሞ ድምጽ ጥሪ ቀርቧል! ተነስ! ተነሺ! ተነሱ!

አማራውን እና የኦርቶዶክስ ሀይማኖትን ከጥፋት እንታደግ!

ኢትዮጵያን ለማዳን ጊዜው ዛሬ ነው!

ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅልን!